# ጠንካራ የትምባሆ ቁጥጥር አንቀፆችን የያዘው አዋጅ ቁጥር 1112/2011

የምግብና የመድኃኒት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 1112/2011 "የትምባሆ ምርት" ማለት በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ ከትምባሆ ቅጠል ተዘጋጅቶ በማጨስ፣ በመሳብ፣ በማኘክ፣ በማሽተት ወይም በሌላ መንገድ የሚወሰድ ማንኛውም ንጥረ ነገር ነው» ይላል ።

ይህ አዋጅ ጠንካራ የትምባሆ ቁጥጥር አንቀፆችን በውስጡ የያዘ ነው። ለአብነት እድሜው ከ21 ዓመት በታች ለሆነ ሰው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የትምባሆ ምርትን መሸጥ ወይም ከ21 ዓመት በታች በሆነ ሰው እንዲሸጥ ማድረግ የተከለከለ መሆኑን በዚህ አዋጅ ተቀምጧል።

በዚህ አዋጅ መሠረት ትምባሆ ማጨስና መጠቀም በተከለከሉባቸው ቦታዎች ቅጥር ግቢ ውስጥና በማንኛውም የጤና ተቋም፣ ትምህርት ቤት የመንግሥት ተቋምና የወጣት ማዕከላት ሙቶ ሜትር ዙሪያ ትምባሆ መሸጥ የማይፈቀድ ሲሆን በዚህም መሠረት የሕዝብ መገልገያ ስፍራዎችን ሙቶ በሙቶ ሊባል በሚችል ደረጃ ከትምባሆ ጭስ ነፃ እንዲሆኑ የሚያስገድድ ነው።

በመሆኑም ማንኛውም ሰው ከበር መልስ ባለ ለሕዝብ ክፍት በሆነ ማንኛውም ቦታ፣ ከበር መልስ ባለ ማንኛውም የሥራ ቦታ፣ በሁሉም የሕዝብ መጓጓዣ እና በጋራ መኖሪያ ቤት በማንኛውም የጋራ መገልገያ ቦታ ላይ ማጨስ ወይም ትምባሆን መጠቀም አይችልም። በዚህም መሠረት ማጨስ ወይም ትምባሆን መጠቀም በተከለከለባቸው ከበር መልስ ባሉ ለሕዝብ ክፍት በሆኑ ቦታዎች እና የሥራ ቦታዎች በአሥር ሜትር ዙሪያ ውስጥ ባለ መግቢያ በር፣ መስኮት ወይም አየር ወደ ውስጥ ሊያስገባ በሚችል ሌላ ቦታ ውስጥ ማጨስ ይከለከላል።

ከዚህ በተጨማሪም በማንኛውም የጤና ተቋም፣ የመንግሥት ተቋም፣ በዋናነት ለሕጻናት እና እድሜው ከ21 ዓመት በታች ለሆነ ሰው አገልግሎት የሚውል ትምህርት ቤትና ከፍተኛ የትምህርት ተቋማትን ጨምሮ ማንኛውም ሌላ ለሕዝብ ክፍት በሆነ ቦታ ላይ፤ በወጣት ማዕከል፣ በመዝናኛ ፓርክ እና ሌላ በአስፈጻሚ አካሉ ወይም በክልል ጤና ተቆጣጣሪው በሚወሰን ከበር ውጭ ባለ ሌላ ቦታ እና ቅጥር ግቢ ውስጥ ማጨስ ወይም ትምባሆ መጠቀም የተከለከለ መሆኑ በማያሻማ መልኩ ተቀምጧል።

ሌላው ማንኛውም ትምባሆ የሚሸጠው ሃያ ሲጋራዎችን በያዘ ባልተከፈተ ፓኬት መሆን እንዳለበትና ሲጋራን በነጠላ ወይም በፍሬ መሸጥ እንደሌለበት ደንግጓል። በተጨማሪም ማንኛውም ሰው የኢንተርኔት፣ የፖስታ እና የቴሌኮሙኒኬሽን ሽያጭን ጨምሮ ሻጭ እና ገዥ በአካል በማይገናኙበት በምንም ዓይነት ሌላ ዘዴ ተጠቅሞ የትምባሆ ምርት መሸጥ፣ እንዲሸጥ ማስቻል ወይም እንዲህ ዓይነቱን ሽያጭ ማመቻቸት የለበትም ይላል።

ከዚህ ባሻገር ለሕዝብ ክፍት የሆነ ቦታ ወይም ማጓጓዣ ባለንብረት ወይም ሌላ ኃላፊነት ያለበት ሰው ወይም የሥራ ቦታን በተመለከተ አሠሪ ወይም ሌላ አግባብ ያለው ሰው በጉልህ የሚታይ ትምባሆ ማጨስ ወይም መጠቀም የተከለከለ መሆኑን የሚገልጽ ማሳሰቢያ ከነባለቀለም ምልክቱ የመለጠፍ ግዴታ ተጥሎበታል።

በተለይ ደግሞ የትምባሆ ምርት ማጨስ፣ መጠቀም ወይም መሸጥ የተከለከለባቸው ቦታዎች ወይም ማጓጓዣ ባለንብረት ወይም ለማስተዳደር ኃላፊነት የተሰጠው ሰው በእነዚህ ቦታዎች የትምባሆ ምርት እንዳይጨስ ወይም ጥቅም ላይ እንዳይውል፣ እንዳይሸጥ እና የሲጃራ መተርኮሻ ወይም ሌላ የትምባሆ ምርትን ለመጠቀም የሚያገለግል ማንኛውም ዕቃ እንዳይቀመጥ ያዛል።

ሌላው አዋጅ ቁጥር 1112/2011 ጠንካራ የትምባሆ ቁጥጥር አንቀፆችን ይዟል ከሚያሰኙት አንቀፆች መካከል አንቀፅ 57 አንዱ ነው። በዚህ አንቀፅ እንደተቀመጠው ማንኛውም የትምባሆ ምርት የውጭ ማሸጊያ አስፈጻሚ አካሉ ማለትም የኢትዮጵያ ምግብና መድኃኒት ባለሥልጣን በሚያወጣው መስፈርት መሠረትና በጊዜ ቀመር የሚቀያየር የጤና ማስጠንቀቂያ ጽሑፍ እና ባለቀለም ምስል በአንድ ላይ መያዝ ያለበት ሲሆን በዚህም መሠረት አስፈጻሚ አካሉ የሚያወጣው መስፈርት የጤና ማስጠንቀቂያውን ለመከበብ የሚውለውን ቦታ ሳይጨምር በትምባሆ ምርቱ የውጭ ማሸጊያ በእያንዳንዱ የፊት እና የኋላ ገጽ ከ70 በመቶ ያላነሰ ቦታ የሸፈነ መሆን አለበት የሚለው ይገኝበታል።

ከዚህ በተጨማሪ የአዋጁ ጠንካራ የትምባሆ ቁጥጥር አንቀፅ ተደርጎ ሊወሰድ የሚችለው አንቀፅ 61 ነው። ይህ አንቀፅ እንደሚለው ማንኛውንም የትምባሆ ምርትን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ማስተዋወቅ፣ ፕሮሞት ወይም ስፖንሰር ማድረግ የተከለከለ ሲሆን በዚሁ አግባብ ማንኛውንም የትምባሆ ምርት ማስተዋወቅ፣ ፕሮሞት ማድረግ ወይም ስፖንሰርሺፕ ማካሄድ፤ እንዲሁም የትምባሆን ምርትን ሊያስተዋውቅ ወይም ፕሮሞት ሊያደርግ የሚችል ነገርን በማንኛውም መንገድ ማተም፣ ማሳተም፣ ማሰራጨት ወይም ተደራሽ ማድረግ፤ የማስታወቂያ፣ ፕሮሞት ማድረጊያ እና የስፖንሰርሺፕ መገልገያን ማሳተም ወይም ተደራሽ ማድረግ፤ በተጨማሪም እንደሚዲያ ወይም ኩነት አመቻች፣ ታዋቂ ሰው ወይም ሌላ ተሳታፊ፣ ማንኛውም የስፖንሰርሺፕ ስጦታ ተቀባይ ወይም እንዲህ ዓይነቱን ስጦታ የሚያመቻች ደላላ በመሆን በማንኛውም የትምባሆ ምርት ማስታወቂያ፣ ፕሮሞት ማድረግ ወይም ስፖንሰርሺፕ ላይ መሳተፍ የተከለከለ ነው።

ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ እና ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣ ሕግ መሠረትም ትምባሆ ማጨስ፣ መጠቀም ወይም መሸጥ በተከለከለበት አካባቢ፣ ማጓጓዣ ወይም ቦታ ትምባሆን የሸጠ እንደሆነ ከስድስት ወር በማይበልጥ ቀላል እስራት ወይም ከብር አምስት ሺ በማይበልጥ መቀጮ እንደሚቀጣ ያስቀምጣል።

ትምባሆ ማጨስ፣ መጠቀም ወይም መሸጥ በተከለከለበት አካባቢ፣ ማጓጓዣ ወይም ቦታ ትምባሆን ያጨሰ ወይም የተጠቀመ እንደሆነ ከብር አንድ ሺ በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል ይላል። በዚህ አዋጅ እና ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣ ሕግ መሠረትም ትምባሆ ማጨስ፣ መጠቀም ወይም መሸጥ በተከለከለበት አካባቢ፣ ማጨስ የተከለከለ መሆኑን የሚገልጽ ጽሑፍ እና ተጓዳኝ ሥዕል ካለጠፈ ወይም ሲጨስ አስፈላጊውን እርምጃ ካልወሰደ ከሦስት ወር በማይበልጥ ቀላል እሥራት ወይም ከብር አንድ ሺ እስከ ብር አሥር ሺ በሚደርስ መቀጮ እንደሚቀጣ በአንቀፅ 67 ቁጥር 20 እና 22 ተቀምጧል።

Tel : +251-11-552-41-22 http://www.fmhaca.gov.et/contact/
+251-11-552-41-22 E-mail contactefda@efda.gov.et
P.o.box. 5681 Telegram channel link
Free call. 8482 https://t.me/ethiopianfoodanddrugauthority/

በብርሃንና ሠላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ